# የሰሜን አሜሪካ የካህናትና የምእመናን አራተኛ ጉባኤ

## በርዕሰ አድባራት ደብረ ሰላም ቅድስት ማርያም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን

## ዋሽንግተን ዲሲ

## ጥቅምት ፳፻፩ ዓ/ም

### የእንኳን ደህና መጣችሁ ንግግር

በአቶ አበበ አቦዬ
የባለአደራዎች ቦርድ ምክትል
ሊቀ መንበር

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ

የተከበሩ የማህበረ ካህናትና ምእመናን ሊቀ መንበር ጸባቴ የማነ ብርሃን
የተከበሩ አባታችን ሊቀ ሊቃውንት ወርቅነህ ሃይሌ
ክቡር ዶ/ር አክሊሉ ሐብቴ
የተከበራችሁ አባቶችና የተከበራችሁ የልዩ ልዩ አብያተ ክርስቲያናት ወኪሎች፣
ሊቃውንተ ቤተክርስቲያን እንዲሁም ውድ ምዕመናንና ምዕመናት

ከሁሉ በፊት ይህ ጉባዔ በተሳካ ሁኔታ ተጀምሮ እንዲካሄድ ለፈቀደ አምላክ ክብርና ምስጋና ይግባው::

በሰሜን አሜሪካ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ለማጠናከር ቤተ ክርስቲያናችንን እያወከ ያለውን የውስጥና የውጭ ችግር ተቋቁሞ መፍትሄ ለማምጣት ለመወያየትና ለመመካከር በወገኖቻችን ላይ እየደረሰ ያለውን ጥቃት ለመቋቋም ለወገን ተገን ሆነን እርዳታ ለመስጠት በዚህ የፍቅርና የሰላም ቦታ በሆነው በእመቤታችን ደብር በመገኘትሁ የተሰማንን ከፍተኛ ክብርና ታላቅ ደስታ እየገለጽን በባለአደራው ቦርድ እንዲሁም በምዕመናኑ ስም እንኳን ደህና መጣችሁ እንላለን::

እንደሚታወቀው ሁሉ ቤተ ክርስቲያናችን የህዝብ ቤተ ክርስቲያን በመሆኗ ከተቋቋመችበት ጊዜ ጀምሮ በፕሮግራም መስፋፋት በመንፈሳዊ አገልግሎት ሙሉ ሰፊነትና የአባልነት ቁጥር መጨመር በንብረት ማከማቸት እንቅስቃሴ ከፍተኛ ግስጋሴ አድርጋ እንዲህ ያለ ሰፊ ቦታ ገዝተን ያለብንን እዳ ከፍለን ለመጨረስ የቀረብን ጥቂት ነው::  አሁን ያለንበት ደረጃ አዲሱን ቤተ ክርስቲያን ለመስራት የህንጻ አሰሪ ኮሚቴን በማደራጀት ላይ ነን:: እናንተም አዲሱን ቤተ ክርስቲያን ለማሰራት በምናደርገው ጥረት ሁሉ እንዲሳካልን እግዚአብሔር እንዲፈቅድልን በጸሎት እንድታሰቡንና በሚያስፈልገው ሁሉ እንድትተባበሩን በዚህ አጋጣሚ ጊዜ ማሳሰብ እንወዳለን::

**የተከበራችሁ የጉባኤው ተሳታፊዎች:-**

ስለቤተ ክርስቲያናችን እንቅስቃሴ የቤተ ክርስቲያኑ አለቃ ሊቀ ማዕምራን ዶ/ር አማረ ካሣዬ ያቀረቡት አጭር መግለጫ  በቂ በመሆኑ ላለመደጋገም መጠነኛም ቢሆን ለተሳታፊዎች ይጠቅም ይሆናል በማለት በቤተ ክርስቲያናችን ሂደት እንደዚህ ያለውን ክንውን እንዴት ሊገኝ ተቻለ?  ለግኙትስ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያዋጡት ምንድን ናቸው? የሚለውን በአጭሩ ለመግለጽ እንወዳለን::

በመሰረቱ ምክንያቶቹ ሶስት ናቸው::

አንደኛውና ዋናው ለዚህ ሁሉ በጎ ስራ ክንውን ልዩ ልዩ የተቀነባበሩና የተደጋገሙ ፈተናዎችን መቋቋም የተቻለው የቤተ ክርስቲያናችን መሪና መሰረት በሆነው በመድሃኒዓለም ጠባቂነት በቅድስተ ቅዱሳን ድንግል ማርያም እርዳታና ምልጃ መሆኑ ነው:: የዚህ የበላይ ጥበቃና ምልጃ ውጤት በመካከላችን ይንጸባረቃል::  በዚህች ቅድስት

ቤተ ክርስቲያን የሚያገለግሉ ካህናትና ምእመናን በመካከላቸው የሚታየው መፈቃቀር መከባበር መቻቻል የዚህ ሁሉ ጸጋ ነጸብራቅ ነው ማለት ይቻላል።

ሁለተኛው የጥንካሬችን ምክንያት በጥንቃቄ ተቀርጾ በህዝብ ጸድቆ በስራ ላይ የሚገኘው የቤተ ክርስቲያናችን መተዳደሪያ ደንብ ነው። የመተዳደሪያ ደንባችን ይዘት ብቻ ሳይሆን መንፈስም ጭምር ነው። የመተዳደሪያ ደንባችን መሰረታዊ አላማ መንፈሳዊ መሆኑን አስተዳደሩ መንፈሳዊ አላማን በስራ ለማዋል የሚረዳ መሆኑን የመንፈሳዊ ጉዳዮችን በተቀዳሚ የሚያከናውኑ ካህናት መሆናቸውን የገንዘብና የንብረት አስተዳደር ጉዳዮችን በተቀዳሚ የሚከታተሉ ምእመናን መሆናቸውን ሁለቱም የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጾች መሆናቸውን የሚመራ ሚዛኑን የጠበቀ መተዳደሪያ ደንብ መኖሩ ነው። ስለሆነም የቤተ ክርስቲያነችን የቦርድ አባላት አቀራረጽ ውስጥ ከምእመናን ሌላ የቤተ ክርስቲያናችን አለቃ በተጨማሪ ካህናትን የሚወክልና በካህናት የሚወከል የሰንበት ት/ቤት ወጣቶችን የሚወክል አባል እንዲካተቱ ተደርጓል። በየሁለት ዓመት ምርጫ ይካሄዳል። ዝርዝር መመሪያዎችን እንደአስፈላጊነቱ ይቀረጻል።

ሶስተኛው የጥንካሪያችን ምክንያት በእውቀታቸውና በጉልበታቸው ነጻ አገልግሎት የሚሰጡ ምእመንና ምእመናት እስተዋጽኦ ነው። በቤተ ክርስቲያኑ አስተዳደር መዋቅር በቦርዱ ስር ሆኖ የሚያገለግል የእለት ተእለት ስራዎችን ከሙሉ ቀን ሰራተኞች ጋር ተባብሮ የሚሰራ በቤተ ክርስቲያኑ አለቃ የሚመራ የስራ አመራር ወይም የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ መኖሩ ነው። የዚህ ኮሚቴ አባላት በቤተ ክርስቲያኑ በተዋቀሩ ልዩ ልዩ የአገልግሎት ኮሚቴዎችን በመሪነቱ በሰብሳቢነት የሚያገለግሉ ምእመንና ምእመናት ናቸው። በአጠቃላይ በዚህና በተመሳሳይ ኮሚቴዎች ውስጥ የነጻ አገልግሎት የሚሰጡ ቁጥራቸው 150 የሚደርስ አባላት ያቀፈ ነው።

**የተከበራችሁ የጉባኤው ተሳታፊዎች፡-**
እርግጠኛ ነን ይብዛም ይነስም እንደዚህ ያለ ወይም ተመሳሳይ የአገልግሎት መዋቅር በየቤተ ክርስቲያናችሁ ውስጥ ይገኛል የሚል ግምት አለን። ስለዚህ እያንዳንዳችን ልምዳችንን ክንውናችንንና የገጠሙን ችግሮች እንዴትስ እንደተወጣነው የመረጃ ልውውጥ ብናደርግ እርስ በርሳችን እንማማራለን በሚል አስተሳሳብ ነው የእኛን የቤተ ክርስቲያን ልምድ በአጭሩ ከዚህ በላይ የገለጽነው።

እንደምትመለከቱትና እንደምትገነዘቡት ይህ የሚያሳየው ከአንዲት ደብር ይህን ያህል አስተዋጽኦ ማድረግ ከተቻለ በሰሜን አሜሪካ ያለነው አብያተ ክርስቲያናት በአንድ ጠረጴዛ ዙሪያ ተቀምጠን ሃይላችንን ካስተባበርን አንድ ከሆንን ከተቻቻልን ከተዋደድን ከተሳሰብንንና ከተፋቀርን ስለሀገር ስለቤተክርስቲያናችን ችግር በመወያየት መፍትሔ እናገኛለን፣ ወገኖቻችንን እንረዳልን፣ የበለጠ ውጤት የሚያሳይ ፍሬ ያለው ስራ ለመስራት እንችላላን የሚል እምነት አለን። ይህንን በማመን ነው ያለማመንታት ይህ ጉባኤ ለሁለተኛ ጊዜ በደብራችን እንዲካሄድ በደስታ የተቀበልነው። በዚህ ታሪካዊ ስብሰባ ታሪካዊ ውሳኔ በመወሰን ውጤት የሚያመጣ እንቅስቃሴ ክትትል የሚያደርግ አካል አቋቋመን እንደምንሰናበት እናምናለን። በዚህ መንፈስ እንድንሰራ እግዚአብሔር ይርዳን።

አበበ አቦዬ
የባለአዳራዎች ቦርድ ምክትል ሊቀ መንበር
ጥቅምት 2001 ዓ/ም